# በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮያውያን የተዘጋጀ ገለጻ

## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሚሊንየም ቦንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ ገለጻ

## ስለ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር ሲሆን የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

- የተቀማጭ ሒሳብ አገልግሎት
- የብድር አገልግሎት
- የወጪና ገቢ ንግድ የፋይናንስ አገልግሎት
- የሐዋላ አገልግሎት
- የወጪና ገቢ ንግድ የፋይናንስ አገልግሎት
- የተለያዩ ሰነዶችና ሌሎች ዋጋቸው ውድ የሆኑ እቃዎችን በአደራ ማስቀመጥ ናቸው::

2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላለፉት 67 ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያገለገለ ባንክ ነው
3. በአሁኑ ሰዓት ያለው የቅርንጫፍ ስርጭት 205 ሲሆን በቅርቡም አዳዲስ ቅርንጫፎችን በመክፈት የቅርንጫፍ አድማሱን ከፍ ያደርጋል
4. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአገራችን ለረጅም ጊዜ የባንኩን ሴክተር እየመራ የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ሰዓትያለው ድርሻ በፐርሰንት ሲታይ

- በተቀማጭ ሒሳብ 65%
- በብድር 35.7 %
- በቅርንጫፍ ስርጭት 53% ይዞ በመምራት ላይ ይገኛል::

5. በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ንግድ ባክ ባጠቃላይ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተሠማሩ ከ8000 በላይ ሠራተኞች አሉት
6. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ራእይ “በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ባንክ መሆን” ሲሆን ይህንን ለማሳካትም በባንኩ አጠቃላይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለውን ጥናት አጠናቆ በመተግበር ላይ ይገኛል

7. በአለም አቀፍ ደረጃ ከ45 በላይ ከሆኑ የውጭ ባንኮች ጋር በመሥራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከዚህም ውስጥ

- ሲቲ ባንክ
- ጄፒ ኤም ሞርጋን ቸዝ ባንክ
- ኤች.ኤስ ሲ.ሲ ባንክ
- ኮሜርዝ ባንክ
- ስቴት ባንክ ኦፍ ኢንድያ
- ደች ባንክና
- ስታንደርድ ባንክ ኦፍ ሳውዝ አፍሪካ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ::

## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልኮርፖሬሽን ሚሊንየም ቦንድ

የቦንዱ ይዘት

- የቦንዱ ዓይነት - ኮርፖሬት ቦንድ
- ቦንዱን ያዘጋጀው - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን
- ወኪል - የ|ትዮጵያ ንግድ ባንክ
- የቦንዱ ስም - ኢ.ኤ.ኃ.ኮ ሚሊኒየም ቦንድ
- ክፍያው የሚከናወነው - በዶላር /ፓውንድ /ዩሮ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚገበያይባቸው ሌሎች የውጪ አገር ገንዘቦች ይሆናል
- የብቁነት መስፈርት - በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ አትዮጵያውያን ብቻ ብቁ ናቸው
- ዝቅተኛ የቦንድ ዋጋ - እያንዳንዱ ቦንድ ባለ 100 የአሜሪካን ዶላር ዋጋ አለው::
- ሆኖም ለመጀመሪያ ጊዜ ዝቅተኛው የግዢ መጠን 500 የአሜሪካ ዶላር ይሆናል::
- የቦንዱ የግዢ ገደብ 5 7 እና 10 ዓመት ይሆናል::
- ቦንዱ የሚከፈልበት ጊዜ - የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ይሆናል::
- ቦንዱ ወለድ የሚከፈለው - በየዓመቱ ይሆናል::
- ዋስትና - የመንግሥት የቦንድ ዋስትና ይሰጣል::
- የገቢ ግብር - ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው::

### የቦንድ ክፍያን በተመለከተ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አማራጮች መጠቀም ይችላሉ

### ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች

1. የክፍያውን ገንዘብ በስዊፍት /SWIFT/ወደ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ
   - ገዢው ክፍያውን በስዊፍት ካስተላለፈ በኋላ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቦንድ ሰርተፊኬት ለገዢው ይልካል ወይም
   - ገዢው ከፈለገ ሠርቲፍኬቱ በባንኩ ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል ።
2. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ውስጥ ከሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ክፍያውን መፈጸም
   - ይህ የባንክ ሒሳብ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚከፍሉት የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ነው።
   - -ገዢው ክፍያውን ከፈፀመ በኋላ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቦንድ ሠርተፊኬቱን ለገዢው በአድራሻቸው ይልካል ወይም
   - ገዢው ከፈለገ ሠርተፍኬቱ በባንኩ ውሰጥ ሊቀመጥ ይችላል።
3. በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመሄድ ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ መፈፀም
   - በጥሬ ገንዘብ ለመክፈል የውጭ ምንዛሪው በሕጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውሰጥ ለመግባቱ ማረጋገጫ ወረቀት አብሮ ማቅረብ ያስፈልጋል።
   - ክፍያው እንደተፈጸመ ባንኩ የቦንድ ሠርተፊኬቱን ለገዢው ይሰጣል።

## ዲያስፖራ አካውንት ምንድን ነው?

- በውጭ አገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በውጪ ምንዛሪ የሚከፍቱት ተቀማጭ ሂሣብ ነው ።
- ይህ ሂሳብ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው በውጭ ምንዛሪ ተቀማጭ ሂሳብ እንዲከፍቱ ያግዛል ።
- ይህን ሂሳብ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች መክፈት ይችላሉ።
- ከሂሳቡ ከሚገኙ ሌሎች ጥቅሞችም በተጨማሪ ይህ ሂሳብ በአገር ውስጥ ገንዘብ ብድር ለማግኘት በዋስትና ያገለግላል።

ሂሳቡን መክፈት የሚቻለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ ነው::

- የአሜሪካን ዶላር
- የእንገግሊዝ ፓውንድ
- ዩሮ

- በቀጣይነት ወደተከፈተው ሂሳብ ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ከላይ ከተጠቀሱት የውጭ ገንዘቦች በተጨማሪ በሌሎች አገሮች ገንዘቦች ማለትም በካናዳ ዶላር በጃፓን የን በሳውዲ ሪያል በአውስትራሊያ ዶላር እና በዩናይትድ ዓረብ ኤሚሬትስ ድርሃም መቀመጥ ይችላል ::
- ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ውጭ በሌሎች የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ከላይ ከተጠቀሱትከሶስቱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ወደ አንዱ ተመንዝሮ ተቀማጭ ይሆናል ::

## የተቀማጭ ሂሣብ ዓይነቶች

❖ አስቀድሞ ለሚወሰን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ የሚሆን ሂሣብ

❖ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ

❖ ወደ ውጭ አገር ሂሣብ ወይም ገንዘብ መዘዋወር የማይችል በብር የሚቀመጥ ሂሣብ

## የብቁነት መስፈርቶች

የዚህ ሂሳብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ

- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን
- በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች
- ከላይ በተጠቀሱት ግለሰቦች በባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች
- ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ነገር ግን በሥራ ምክንያት በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ በቂ ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉ አስፈላጊ ሠነዶች:
- በትክክል የተሞላ እና በሂሣብ ከፋቹ የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ፣
- ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣
- በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሰዱበት አገር መታወቂያ፣
- ለድርጅት አመልካቾች የባለቤትነት ማስረጃ እና የድርጅቱ የመመስረቻ ሠነድ ናቸው::

በአሁኑ ሰዓት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመሥራት ላይ የሚገኙ የሐዋላ ድርጅቶች እነማን ናቸው

- ገንዘብ ወደሀገራችን በህጋዊ መንገድ የሚገባበትን ሁኔታ ለማበረታታት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጣውን አዋጅ ተከትሎ ባንካችን ከዚህ በፊት ከዌስተርን ዩኒየን ጋር ብቻ ተገድቦ የነበረውን የሐዋላ አገልግሎት በማስፋት በአሁኑ ሰዓት ከ9 በላይ የሐዋላ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ጋር በመሥራት ላይ ሲሆን በቅርቡም ከአራት ተጨማሪ ድርጅቶች ጋር ሥራ ለመጀመር ዝግጅቱን አጠናቋል::